የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ ሦስተኛ ዓመት ቁጥር ፵፫
አዲስ አበባ ግንቦት ፳፱ ቀን ፪ሺ፱ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

23rd Year No.43
ADDIS ABABA 6th June, 2017

**ማውጫ**

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፲፫/፪ሺ፱ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በኬንያ ሪፐብሊክ መንግስት መካከል በስታንዳርድ የባቡር ሃዲድ መስመር ዝርጋታ፣ አሰራር እና አስተዳደር ዙሪያ ለመተባበር የተደረገዉን የሁለትዮሽ ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ................................ገጽ ፱ሺ፮፻፶፯

**Content**

Proclamation No. 1013/2017

Agreement between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the Republic of Kenya for the development, operation and management of standard gauge railway network ratification Proclamation ..............................……..….. --Page 9657

## አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፲፫/፪ሺ፱ ዓ.ም

## በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በኬኒያ ሪፐብሊክ መንግስት መካከል በስታንዳርድ የባቡር ሃዲድ መስመር ዝርጋታ፣ አሰራር እና አስተዳደር ዙሪያ ለመተባበር የተደረገዉን የሁለትዮሽ ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በኬንያ ሪፐብሊክ መንግስት መካከል የካቲት ፳፪ ቀን ፪ሺ፬ ዓ.ም በስታንዳርድ የባቡር ሃዲድ መስመር ዝርጋታ፣ አሰራር እና አስተዳደር ዙሪያ የትብብር ስምምነት በናይሮቢ የተፈረመ በመሆኑ፤

ይህንኑ ስምምነት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የህዝብ ተወካዮች ም/ቤት ግንቦት ፲፭ ቀን ፪ሺ፱ ዓ.ም ባካሄደው ስብሰባ ያፀደቀው በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሰት አንቀጽ ፶፭ /፩/ እና /፲፪/ መሰረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

## PROCLAMATION NO. 1013 /2017

## A PROCLAMATION TO RATIFY THE BILATERALAGREEMENT BETWEEN THE GOVERNMENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE GOVERNMENT OF THE REPUBLIC OF KENYA FOR THE DEVELOPMENT, OPERATION AND MANAGEMENT OF STANDARD GAUGE RAILWAY NETWORK

**WHEREAS,** the Bilateral Agreement between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the Republic of Kenya for the development, operation and management of standard gauge railway network was signed in Nairobi on the 1st day of March 2012;

**WHEREAS,** the House of peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified the said Agreement at its session held on the 23rd day of May, 2017;

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Article 55 (1) and (12) of the Constitution, it is hereby proclaimed as follows:

**፩. <u>አጭር ርዕስ</u>**

ይህ አዋጅ ‹‹በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በኬንያ ሪፐብሊክ መንግስት መካከል በስታንዳርድ የባቡር ሃዲድ መስመር ዝርጋታ፣ አሰራር እና አስተዳደር ዙሪያ ለመተባበር የተደረገዉን የሁለትዮሽ ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፲፫/፪ሺ፱›› ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

**፪. <u>ስምምነቱ ስለመፅደቁ</u>**

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በኬንያ ሪፐብሊክ መንግስት መካከል የካቲት ፳፪ ቀን ፪ሺ፬ ዓ.ም በስታንዳርድ የባቡር ሃዲድ መስመር ዝርጋታ፣ አሰራር እና አስተዳደር ዙሪያ ለመተባበር የተደረገዉ የሁለትዮሽ ስምምነት በዚህ አዋጅ ፀድቋል፡፡

**፫. <u>አስፈፃሚ አካላት</u>**

ይህን ስምምነት እንዲያስፈፅም የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ትራንስፖርት ሚኒስቴር በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል፡፡

**፬. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ግንቦት ፳፱ ቀን ፪ሺ፱ ዓ.ም**

**ሙላቱ ተሾመ (ዶ/ር)**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

**1. <u>Short Title</u>**

This Proclamation may be cited as the “Agreement between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the Republic of Kenya for the development, operation and management of standard gauge railway network ratification Proclamation No.1013/2017’’

**2. <u>Ratification of the Agreement</u>**

The Bilateral Agreement between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the Republic of Kenya for the development, operation and management of standard gauge railway network, signed in Nairobi on the 1st day of March, 2012 is hereby ratified.

**3. <u>Implementing Organs</u>**

The Ministry of Transport of the Federal Democratic Republic of Ethiopia is hereby empowered to implement the Agreement.

**4. <u>Effective Date</u>**

This Proclamation shall come into force upon publication on the Federal Negarit Gazettee.

**Done at Addis Ababa on this 6th day of June, 2017.**

**MULATU TESHOME (Dr.)**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OFETHIOPIA**